በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥቅምት ፳ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

***ክርስትና በሮም እንዴት ተመሠረተ?***

- ሮሜ የሮም መንግሥት ዋና ከተማ ነበረች፡፡ በከተማዋ በነበሩት ቅጥሮች ውስጥና ውጪ ብዙ ቤቶች ተሠርተው ከተማዋ የተስፋፋች ሆና ነበር፡፡
- ሮሜ የዓለም የፖለቲካ ሰዎች፣ መሪዎች መናኸሪያና እንዲሁም የሳይንስ፣ የአርትና የፍልስፍና ትምህርቶች የሚሰጡባቸው በርካታ ትምህርት ቤቶች የሚገኙባት ከተማ ነበረች፡፡ ዛሬም ድረስ በበርካታ ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠው የሮም ሕግ ከተማዋን ታዋቂነትዋን አጉልቶታል፡፡
- ሮም የብዙ አገር ዜጎች መስተንግዶ የሚያገኙባት ከተማ ከመሆንዋ የተነሳ ጣዖታትን እያመለኩ ከምግባር የወጣ ድርጊት የሚፈጽሙ በርካታ ሰዎች ይገኙባት ነበር፡፡ በምዕራፍ አንድ የተጠቀሰውም ጉዳይ ይኸው ነው፡፡
- በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በሮም የሚኖሩ ነዋሪዎች ቁጥር ከ1.5 ሚሊዮን ይበልጥ ነበር፡፡ ከሕዝቡም ቁጥር አንድ ሦስተኛው ምግባር የጎደለው ነበር፡፡
- በከተማዋ ከሚገኙት ሌሎች ሕዝቦች ጋር አይሁድም ይገኙ ነበር፡፡ ከእነዚህ አይሁድ የሚበዙት በ63 ከክ.ል.በፊት ፓምፔ በሚባለው ጦረኛ ሰው ድል ተመተው ሶርያን በተቆጣጠረ ጊዜ ተማርከው ወደ ሮም የተወሰዱና ከከተማዋ በአንደኛው ጫፍ እንዲኖሩ ግዴታ የተጣለባቸው ነበሩ፡፡
- እነዚህ አይሁድ በጊዜ ብዛት ነጻነት አግኝተው ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን በጻፈ ጊዜ ቁጥራቸው ወደ አሥራ ስድስት ሺ ደርሶ ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

- እነዚህ በሮሜ የሚገኙ አይሁድ በ19ዓ.ም. በጢባርዮስ ቄሳር ዘመን ከደረሰባቸው ነገር ውጪ ተደላድለው በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡
- በ34 ዓ.ም. በቀላውዴዎስ ቄሳር ዘመነ መንግሥት ከሮም ለቀው እንዲወጡ ተገደው ነበር፡፡ ‹‹በወገኑም የጳንጦስ ሰው የሚሆን አቂላ የሚሉትን አንድ አይሁዳዊ አገኝ፤ እርሱም ከጥቂት ጊዜ በፊት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር ከኢጣልያ መጥቶ ነበር፥ አይሁድ ከሮሜ ይወጡ ዘንድ ቀላውዴዎስ አዞ ነበርና፤ ወደ እነርሱ ቀረበ፡፡›› *የሐዋ 18፡2፡፡*
- አይሁድ ከአሥራ ሦስት ሺ በላይ ጉባኤያት የነበሯቸው ሲሆን እነዚህም ጉባኤያት በመካከላቸው መለያየትና አመጽ እንዲሰለጥን ምክንያት ሆኖ ነበር፡፡
- የክርስትና እምነት እንዴት ወደ ሮም እንደገባ እንዲሁም የመጀመሪያው የሮሜ ክርስቲያን ማን እንደሆነ የተገለጸ ነገር ባይኖርም በዚህ ጉዳይ መነሻነት የሚከተሉትን መመልከት እንችላለን፡-
    1. በበዓለ ጰንጠቆስጤ በኢየሩሳሌም ከተሰበሰቡት መካከል ከሮም የመጡ እንደነበሩ ተጽፎልናል፡፡ *የሐዋ 2፡10፡፡* እነርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማመን ተጠመምቀው ክርስቲያኖች በመሆን ወደ አገራቸው ተመልሰው ክርስናን ለወገኖቻቸው ሰብከዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን እስከጻፈበት ዘመን ድረስ በሮም በነበረችው ቤ/ክ ወደ ክርስትና የገቡት አይሁድ ቁጥር ወደ ክርስትና ከገቡት አሕዛብ ቁጥር ይበልጥ ስለነበር የሮም ቄሳሮች ክርስትናን ከአይሁዳዊነት ተከፍሎ የወጣ ክንፍ አድርገው ይቆጥሩት ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

2. የሮም መንግሥት ከአገሪቱ የተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ዋና ከተማዋ ሮሜ መንቀሳቀስ የሚያስችል የነጻነት መብት ለዜጎቹ በመስጠቱ የሚታወቅ ከመሆኑ ጋር ከተማዋ ሮሜም ታላላቅ መሪዎች፣ ምሁራንና ነጋዴዎች የሚበዙባት ነበረች፡፡ እነዚህም አስቀድመው ከአይሁድ ወይም ከአሕዛብ ወገን ሆነው ወደ ክርስትና የመጡ ክርስቲያኖች መሆናቸው የማይጠረጠር ነበር፡፡ እነርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው ስለእምነታቸው በፍጹም ቅንዓትና ጽንዓት ምስክርነታቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል ቅዱስ ጳውሎስ በኤጂያን፣ በመቄዶንያ፣ በግሪክና በታናሽ እስያ ሲያስተምር የሰሙና ወደ ማመን የተመለሱ ይገኙበታል፡፡ እነርሱም ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም ከመሄዱ አስቀድሞ በላከው መልዕክት በላከላቸው ሰላምታ ስማቸው በመጠቀሱ ደቀ መዛሙርቱ እንደነበሩ ታውቀዋል፡፡
3. ንጉሥ ቀላውዴዎች የሚበዙትን ብሎም ሁሉንም አይሁድ ከሮሜ ለማባረር ትዕዛዝ ባወጣ ጊዜ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በኋላ ወደ ሮም ቢመለሱም ወደ ሌሎች ከተሞች ሄደው ለመኖር ግን ተገደው ነበር፡፡ ከእነርሱም መካከል አቂላና ጵርስቅላ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በማመን ክርስቲያኖች ሆነው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ለመገናኘት ችለው ነበር፡፡ *የሐዋ 18፡1-2፡፡* እነርሱም ከቅዱስ ጳውሎስ የክርስትና እምነትን፣ ድንኳን መስፋትን… ተምረው ነበር፡፡ እነርሱና እንደነርሱ ያሉት የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ታላቅ ሚና ነበራቸው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

4. የሮሜ መልዕክት እስከተጻፈበጽ ጊዜ ድረስ ከሐዋርያት አንዳቸውም ቤተ ክርስቲያንን በሮም እንደመሠረቱ አልተጻፈልንም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ወደሮሜ ሄዶ ለማስተማር ቢወድም ስንት ጊዜ እንደተከለከለና ከርሱም ቀድሞ ሌላ ሐዋርያ እንዳላስተማረ ጽፎልናል፡፡ *ሮሜ 15፡20፣ 1፡9፣ 1፡19፣ 15፡22-24፡፡*
5. ቅዱስ ጳውሎስ ከአሕዛብ የተላከ መልዕክተኛ እንደሆነ ‹‹ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ፡፡›› *ገላ 2፡7፡፡* በማለት ተናግሯል፡፡ ሮምም የአሕዛብ ከተማ ስለነበረች የማስተማር ዕጣ ደርሶት የአገልግሎቱ መናኸሪያ አደረጋት፡፡ *ሮሜ 1፡13-14፡፡*
6. የምሥራቅም ሆኑ የምዕራብ ሊቃውንት ‹‹ቅዱስ ጵጥሮስ የሮምን ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ 25 ዓመት በመንበሩ ተቀምጧል፡፡›› የሚሉትን ሰዎች አስተሳሰብ አይቀበሉትም፡፡ በርግጥም ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት የመጀመሪያው ሲኖዶስ እስከተደረገበት እስከ 50 ዓ.ም. ድረስ በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ *የሐዋ 15፡፡* በ55 ዓ.ም. በአንጾኪያ የነበረ ሲሆን ከቅዱስ ጳውሎስም ጋር በዚያው ተገናኝተዋል፡፡ *ገላ 2፡11፡፡* ቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልዕክቱን በ60 ዓ.ም. ገደማ ሲጽፍ በባቢሎን ነበር፡፡ *ቀዳ ጴጥ 5፡13፡፡* ቅዱስ ጴጥሮስ ቤ/ክንን በ41 ዓ.ም. በሮም መሥርቶ ቢሆን የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት መጻፍ ባላስፈለገው ነበር፡፡ አስፈልጎም ቢሆን በመልዕክቱ የቅዱስ ጴጥሮስን ስም እያነሳ ሰላምታ ይሰጠው ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች

### መልዕክቱ የተጻፈበት ዘመንና ቦታ

- ሐዋርያው መልዕክቱን ወደ እስጳንያ በሚያደርገው ጉዞ መካከል በሮሜ አድርጎ በማለፍ ወደ ሮሜ ለመሄድ ባሰበ ጊዜ ጽፎታል፡፡ ሮሜ 15፡23-24፡፡
- ይህም የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ድሆች ሲል በመቄዶንያና በአካይያ ከሚገኙ ክርስቲያኖች የሰበሰበውን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄደ በኋላ ነው፡፡ ሮሜ 15፡25-26፣ ቀዳ ቆሮ 16፡2፣ ካል ቆሮ 8፡1-4፡፡
- ስለዚህ የሮሜ መልዕክት የተጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ባደረገው ሦስተኛው ጉዞ ጋይዮስ በተባለው ሰው ቤት ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ጋይዮስን ‹‹የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አስተናጋጅ›› በማለት ጠቅሶታል፡፡ ሮሜ 16፡23፡፡
- ጋይዮስ ቅዱስ ጳውሎስ ካጠመቃቸው ከሁለቱ አንዱ ነበር፡፡ አብሮት የተጠመቀውም ቀርስጶስ ይባል ነበር፡፡ ቀዳ ቆሮ 1፡14-15፡፡ መልዕክቱንም ለጤርጥዮስ አድርጎታል፡፡ሮሜ 16፡22፡፡
- መልዕክቱን ወደ ሮም ያደረሰችው በክንክራኦስ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናይት በመሆን ታገለግል የነበረች ፌቤን የተባለች ሴት ናት፡፡ ሮሜ 16፡1፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም የሄደው በ58 ዓ.ም. ፀደይ ወቅት ሲሆን መልዕክቱም ከ57-58 ዓ.ም. እንደተጻፈ ብዙ ሊቃውንት ይስማሙበታል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

***መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች***

***በመጀመሪያይቱ የሮም ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ምዕመናን***

- አባታችን ከሚባለው ከአብርሃም ጀምሮ በርካታ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን እየጠቀሰ የጻፈላቸውና ከቤተ አይሁድ ወደ ክርስትና የተመለሱ አይሁድ ከክርስቲያኖች ምዕመናን ወገን ነበሩ፡፡ *ሮሜ 4፣ ሮሜ 9፡፡*
- ቅዱስ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ተብሎአልና ወደ ክርስትና የገቡ ቤተ አሕዛብም ከክርስቲያኖች ምዕመናን ወገን ነበሩ፡፡ ***ሮሜ 1፡5-7 ፣ ሮሜ 1፡12-14 ፣ ሮሜ 11፡11-13 ፣ ሮሜ 15፡16 ፣ ሮሜ 6፡19፡፡***
- ሌሎቹ ከአይሁድም ከአሕዛብም ወገን ሆነው ወደ ክርስትና የገቡ ናቸው፡፡
- በአጠቃላይ ሮሜ አይሁድ በቁጥር ቢበዙም ከአሕዛብም ከአይሁድም ወገን ወደ ክርስትና የገቡ የሚገኙባት ነበረች፡፡

***የመልዕክቱ ዓላማና አስፈላጊነት***

- ይህ መልዕክት በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታላቅ ሥፍራ የተሰጠው ሲሆን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በሳምንት ሁለት ጊዜ ያነበው እንደነበር ተናግሯል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች

***የመልዕክቱ ዓላማና አስፈላጊነት …***

- ይህ መልዕክት በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታላቅ ሥፍራ የተሰጠው ሲሆን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በሳምንት ሁለት ጊዜ ያነበው እንደነበር ተናግሯል።
- መልዕክቱን ስናጠናው ለምን እንደተጻፈ፣ ወደ ክርስትና የገቡ አይሁድን ነገር፣ የተማሩ ነገር ግን ምግባር የጎደላቸው የሆኑ ከግሪክ የመጡ የአሕዛብ ምሁራንን፣ ሁሉም ባንድ መንፈስ አንድ ልብ ሆነው መኖር እንደሚገባቸው፣ አይሁድ የበላይነት ስሜታቸውን መተው የቸገናቸው መሆናቸውን፣ አይሁድ ለዘራቸው፡ ለባሕላቸው፡ ለአይሁዳዊ ሃይማኖታቸው ከነበራቸው የከረረ ዝንባሌ የተነሳ ክርስቲያን የሆኑ አሕዛብን እንዴት ያስጨንቁ እንደነበር፣ … ወዘተ እንረዳለን።
- አይሁድ የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው ለአብርሃም የተገባለት ቃል ወራሾች ነን፣ የሙሴን ሕግ ለመቀበል በመመረጣቸውም ከሌሎች ሕዝቦች ይልቅ የምንሻል እኛ ነን፣ … በማለት ራሳቸውን ብቻ የእግዚአብሔር ምርጦች አድርገው ያስቡ ነበር።
- አስተሳሰባቸውም የአብርሃም ልጅነትን፣ የተሰጣቸውንም ሕግ ምንነትና እግዚአብሔር ሕዝቡን የመረጠበትን ትክክለኛ ምክንያት ያለመረዳት የሌለበት ስለነበር ክርስትናን ተቀብለውም ከክርስቲያኖች ሁሉ በላይ ከፍ ያለ ሥፍራ ይገባናል ብለው ያስቡ ነበር።
- አሕዛብም በፊናቸው ተቃራኒ ሐሳብ ይዘው ተነሥተው ነበር። አይሁድ የሚደነቁ ሕዝቦች አይደሉም፡ በሩ የተዘጋባቸው ስለሆኑ እንደ አሕዛብ በሩ የበለጠ ክፍት እንዳልተደረገላቸው አሕዛብ ያስቡ ነበር።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

***መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች***

***<u>የመልዕክቱ ዓላማና አስፈላጊነት …</u>***

- ይህም አስተሳሰብ አህዛብን እንደ ኤአሁድ ባለ ትምክህት እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡
- ስለዚህም የሮሜ መልዕክት የእምነትና የመንፈሳዊነትን ተዛምዶ፣ ክርስትናን በሥራ የመግለጥ አስፈላጊነት ለሁለቱም ወገኖች እንዲየስረዳ ሆኖ ተጻፈ፡፡
- በክርስትና እምነት የሚገኝ ሥራ በየዘመኑ በምትኖረው ቤተ ክርስቲያን ሊገለጥ የሚገባው ስለሆነ በእምነት ሆነው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እምነታቸውን በሥራ ለሚገልጡ በሩ በስፋት የተከፈተላቸው መሆኑን መልዕክቱ ይናገራል፡፡
- ሐዋርያው እምነትና መዳንን የሚያገናኛቸው ፍሬ ነገር ምን እንደሆነ ገልጦ ሲጽፍ ለዓለም ሁሉ በተሰቀለው በጌታችን ፍቅር የታተመው ሐዋርያነቱ የሰውን ዘር ሁሉ ለመውደድ እንዳበቃው ገልጧል
- ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስባቸውን ትምክህተኝነት አስመልክቶ ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ ጽፎላቸዋል፡፡
- በእምነት የደከሙትንም አስመልክቶ ርኅራኄን እያደረጉ እምነትን በሥራ መግለጥ እንደሚያስፈልግና በማኅበራዊ ሕይወትም ክርስቲያኖች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባብ በመንፈሳዊነት ቢወጡ በዚህ ዓለም የያዙት ቅድስና በመጨረሻ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር እንደሚያበቃቸው አስረድቷል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

***የመልዕክቱ ዓላማና አስፈላጊነት ...***

- አንዳንዶች መልዕክቱ የሕግን ተግባራዊነት ብቻ ለሚደግፉ አይሁድ የተጻፈ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ አሕዛብንና አይሁድን ለማስታረቅ የተጻፈ ነው ብለውታል፡፡ ሐዋርያው ግን ክርስትና በወንጌሉ በተሰበከበት መልኩ የቅድስናን ሕይወት መያዝን የሚሻ መሆኑን ጻፈ፡፡ መልዕክቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች ይባላል፡፡
- ሐዋርያው መልዕክቱን ሲጽፍ በሮሜ ያለውን ሁኔታ ከደቀመዛሙርቱ ከተረዳ በኋላ በእስጳንያ አድርጎ ወደ ሮሜ ከመሄዱ በፊት ለችግሮቻቸው መፍትሔ እንዲኖራቸው አድርጎ ጻፈላቸው እንጂ ጠባብ አመለካከት ከነበራቸው አይሁድም ሆነ አሕዛብ ጋር ወደ ጠብ አልገባም፡፡
- የሮሜ መልዕክት እምነትና ያለዋጋ በነጻ በጌታችን መሥዋዕትነት ስለተደረገልን መዳን፣ መዳኑም ለሁሉ ስለመሆኑ፣ ስለ ጸጋ፡ ፍርድና ቅድስና፣ ነጻ ፈቃድና ምርጫችንን አስመልክቶ ሰፊ መሠረት ያለው ትምህርት የምናገኝበት ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

***መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች***

***በመልዕክቱ ላይ ጠያቂዎች የሚነሱት ጥያቄ***

- ጠያቂዎች ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክት ላይ የሚያነሱት ጥያቄ የመልዕክቱ አስራ ስድስተኛ ምዕራፍ ለኤፌሶን ሰዎች የተጻፈ ነው የሚል ነው፡፡ ለዚህም ስድስት ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ እነርሱም

1. ሐዋርያው ረጅም ጊዜ ያገለገለው በኤፌሶን ሲሆን ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ግን ሳያያቸው ሳይጎበኛቸው ለብዙዎች ምዕመናን ሰላምታ በመስጠት ጽፎላቸዋል የሚል ሲሆን ምላሹም ሐዋርያው በአካል ተገናኝቶ ለሚያውቃቸው ብቻ ሰላምታ የሚልክበት የተለየ አሠራር የሌለው መሆኑን መረዳት ነው፡፡
2. አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ላለችው ቤት ክርስቲያን በማለት የተጻፈላቸው ወደ ሮም ከተጻፈው መልዕክት ቀደም ብሎ የተጻፈ ሲሆን እነርሱም በኤፌሶን ይኖሩ እንደነበር *ቀዳ ቆሮ 16፡19*፣ ሁለተኛው ጢሞቴዎስ ሲጻፍም በኤፌሶን እንደነበሩ እናውቃለን *ኳል ጢሞ 4፡19* ይህም ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ለሰማዕትነት ተዘጋጅቶ የሚጠብቅበት ጊዜ ነበር ታዲያ በሮም እንደሆኑ አድርጎ እንዴት ይጽፍላቸዋል? ይላሉ፡፡ ለዚህም ምላሹ እንደ ብዙዎች ባለጠጋ አይሁዶች አቂላና ጵርስቅላም ባለጠጋና ቅዱሳን ነበሩ፡፡ በብዙ ቦታዎች የንግድ ድርጅቶች ስለ ነበሩአቸው በሮምና በኤፌሶን የሚገኙትንም ቤቶቻቸውን ለቤተ ክርስቲያን ሰጡ፡፡

# <u>የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች</u>

***መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች***

***<u>በመልዕክቱ ላይ ጠያቂዎች የሚነሱት ጥያቄ</u>***

2. … ሌላው ቀላውዴዎስ ቄሳር አይሁድን ከሮም እንዲወጡ ሲያስገድድ ንግዳቸውን እንዲቆጣጠርላቸው ለሮማዊ ሰው አደራ ሰጥተው ወደ ሮም እስኪመለሱ ድረስ ማስጠበቃቸውን መረዳት ነው፡፡
3. አጤኔጦን በአካይያ የተገኘ የመጀመሪያ ተብሎ ከተነሳ የሚሆነው ለሮም ሳይሆን ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ነው ይላሉ፡፡ *<u>ሮሜ 16፡5፡፡</u>* <u>ምላሹም</u> አጤኔጦን ቅዱስ ጳውሎስ በታናሽ እስያ አገልግሎቱ ያገኘው የመጀመሪያ ፍሬው ሲሆን ከእርሱ እንደተማረው እያስተማረ እንዲኖር ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም ስላልሄደ አጤኔጦን በፍጹም ቅንዓትና ጽንዓት በሮም እንዲያገለግል ያሳሰበው መሆኑ ነው፡፡
4. አንዳንዶች ደግሞ በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን የነበረችው ፌቤን ምዕመናኑን ከማያውቃቸው ወገን ሳትሆን ከሚያውቃቸው ወገን ናት ይላሉ፡፡ <u>ምላሹም</u> ቅዱስ ጳውሎስ በአካል ባያገኛቸውም የርሱን ነገር፣ ለአገልግሎቱም ያለውን ቀናኢነት ሊያውቁ የሚችሉበት ብዙ ዕድል የነበረ ከመሆኑ አንጻር አባታዊ ምክሩን፣ መመሪያውንና መልዕክቱን የሚቀበሉበት ዕድል እንደ ነበራቸው መገንዘብ ነው፤ የሐዋርያው ስምና አገልግሎቱ በስፋት ይታወቅ ነበርና፡፡
5. *<u>በሮሜ 16፡17-19</u>* ‹‹ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፥ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ፡፡ መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአልና፤ እንግዲህ በእናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ፡፡›› በማለት የተጻፈው

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

**መግቢያ - ወደ ሮሜ ሰዎች**

***<u>በመልዕክቱ ላይ ጠያቂዎች የሚነሱት ጥያቄ</u>***

5. መልዕክት ኃይለ ቃል እስከ ምዕራፍ 15 ድረስ ካሉት መልዕክታት ጋር ተያያዥነት ያለው አይመስልም ይላሉ፡፡ ለዚህም <u>ምላሹ</u> የአይሁድን አስተምህሮ የሚከተሉ ቡድኖች ላሉባቸው ችግሮች ጤናማ የሆነ ምላሽ መስጠቱ ነው፡፡ ከሥነ መለኮት አስተምህሮ አንጻር ወደ ክርስትናው የመጡትን አይሁድ ሳያሳጣ ትክክለኛውን ምላሽ በሰላማዊ መንገድ በጥንቃቄ መጻፉን መረዳት ነው፡፡
6. አስራ አምስተኛው ምዕራፍ ‹‹የሰላምም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡›› በማለት ስለተጠናቀቀ አስራ ስድስተኛው ምዕራፍ ከኤፌሶን ገብቶ መቀጠር አለበት፡፡ ለዚህ <u>ምላሹም</u> በሥነምግባር የሚገለጥ የክርስትና ሕይወትን አስመልክቶ የጀመረውን መልዕክት ለማጠቃለል በአሥራ ስድስተኛው ምዕራፍ በሮም ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ለይቶ አትኩሮት ሰጥቶ መጻፉን የሚያመለክት እንደሆነ መረዳት ነው፡፡

- በአጠቃላይ ምዕራፍ 16 ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተላከ መልዕክት ነው የሚለው አስተሳሰብ የሰዎች ጽንሰ ሐሳብ እንጂ ምንም ታሪካዊ መሠረት የሌለው እንደሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡ በሁሉ ማስተዋሉን አምላካችን እግዚአብሔር ያድለን፡፡ አሜን!!!

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org